# ከኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል

## ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

# የሰሜኑ የንፋስ ኃይል ማመንጫ -አሸጎዳ

(ክፍል ሁለት)

ውድ አንባብያን! ባለፈው ሳምንት ዝግጅታችን የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ካስገነባቸው የንፋስ ኃይል ማመንጫዎች መካከል ግንባርቀደም ስለሆነው የአሸጎዳ የንፋስ ኃይል ማመንጫ ከፊል የሥራ እንቅስቃሴ ማስነበባችን የሚታወስ ነው።በዛሬው ክፍል ሁለት ዝግጅታችንም ቀሪ ጉዳዮችን ልናስነብባችሁ ወድደናል።መልካም ንባብ።

እንደሚታወቀው የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ከሀገራችው አልፈው በተለይም በአፍሪካ ገበያ ውስጥ ተወዳዳሪ መሆን የሚችሉ ብቁ ሙያተኞችን ለማፍራት ራዕይ ሰንቆ የሚሠራ እንደመሆኑ፤ በተለያዩ የኃይል ምንጭ አማራጮች ፣ በማከፋፈያ ጣቢያዎችና በከፍተኛ ኪሎቮልት መስመር ዝርጋታዎች የተሠማሩ ሙያተኞችን እያበቃ ይገኛል። ከዚሁ ጋር በተያያዘ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በራሱ የሰው ኃይል የጥገና ሥራዎችን በማከናወን ከፍተኛ ወጪን እየታደገ ስለመሆኑ ከተለያዩ የኃይል ማመንጫ እና ማከፋፈያ ጣቢያዎች ያገኘነው ተሞክሮ ያስረዳል።የአሸጎዳ የንፋስ ኃይል ማመንጫ ጣቢያም በራሱ የሰው ኃይል ባከናወናቸው የጥገና ሥራዎች ውጤታማ የሆኑ ተግባራትን ፈጽሟል።

የንፋስ ኃይል ማመንጫ በሀገራችን መተግበር ከጀመረ አጭር እድሜን ያስቆጠረ ቢሆንም ቴክኖሎጂውን ተላምደው ለብልሽቶች አፋጣኝ ምላሽ የሚሰጡ ሠራተኞችን ማፍራት ተችሏል።ሠራተኞች በልምድ ልውውጥ፣ በስልጠና በሌሎችም አማራጮች አቅማቸውን እንዲገነቡ ተቋሙ የሚያደርገው እገዛና የያዘው ጠንካራ አቋም ለተገኘው ውጤት ወሳኝ ጉዳይ ተደርጎ ይታያል።

በአሸጎዳ ንፋስ ኃይል ማመንጫ ጣቢያ የሠራተኞችን ክህሎት በማሳደግ የተሻለ አቅም ያለው ሙያተኛ ለማፍራት የተለያዩ ተግባራት



አቶ ካህሰ ፀሐይ

ተከናውነዋል። ለሰራተኞች ምቹ ከባቢያዊ የሥራ ሁኔታን ከመፍጠርና አቅማቸውን ከማሳደግ አኳያ በበጀት ዓመቱ 9 ወራት የተለያዩ ተግባራት መከናወናቸውን አቶ ካህሰ ይገልጻሉ።ጣቢያው 166 ቋሚና 14 ጊዚያዊ በድምሩ 180 ሰራተኞች ያሉት ሲሆን ለሠራተኞች ክህሎታቸውን ማሳደግ የሚያስችል የስልጠና መርሃ ግብር በማዘጋጀት ከአዳማ ንፋስ ኃይል ማመንጫ በመጡ ባለሙያዎች አማካኝነት የልምድ ልውውጥ እና የሥራ ላይ ሥልጠናዎችን መስጠቱን ኃላፊው ያስረዳሉ፡፡

የሠራተኞችን ክህሎት በማሳደግ የተሻለ አቅም ያለው ሙያተኛ ለመፍጠር እንዲያስችል ሰራተኞችን በቡድን በማዋቀርና በሃሳብ የመረዳዳት ባህላቸው እንዲዳብር በማድረግ ሥራዎችን በአግባቡ እንዲያከናውኑ ማድረግ ተችሏል ይላሉ። በሥራ ላይ የሚያጋጥሙ አዳዲስ ችግሮች ሲኖሩም ሰራተኛው አስፈላጊ ዶክመንቶችን በማንበብ፣ ከኢንተርኔት በመፈለግና ከጣቢያው ማኑዋል ጋር በማዛመድ እርስ በእርስ በመወያየት ችግሮችን በአጭር ጊዜ የመፍታት ባህሉ እያደገ መምጣቱን አቶ ካህሰ ይገልጻሉ።የሁሉንም ሰራተኞች አፈፃፀም በመለካትና ክፍተቶችን በማረም እንዲሁም ከኃይል ማመንጫዎች የሚወርዱ መመሪያዎችን በመተግበር በአሁኑ ወቅት የኦፕሬሽንና የጥገና ሥራው ሙሉ በሙሉ በጣቢያው ሠራተኞች የሚከናወን እንደሆነ ጠቅሰው ፤ በጣቢያው የተከናወነው የአቅም ግንባታ ሥራ ፍሬ ያስገኘ ስለመሆኑ ያስረዳሉ።

በነበረው የጸጥታ ችግር ወቅት ከብሔራዊ የኃይል ቋት ውጭ ሆኖ ከአንድ ዓመት በላይ በመቆየቱ ምክንያት በተርባይኖች ያጋጠመውን የባትሪዎች ችግር በተወሰኑት ላይ የመቀየር፣ የተርባይን ክንፍ አንግልና ስሊፕሪንግ የማስተካከል ሥራ መከናወኑን ኃላፊው ያብራራሉ። የኮንቨርተር ካርድ ፊት ቦርድ፣ ከፌዝ 2/3 ተርባይን የኃይል ማስተላለፍያ መስመር ቁጥር 3 ከ 4 KM በላይ የሆነው 33 KV አጋጥሞት ለነበረው ጉዳት የጥገና እንዲሁም በማከፋፈያ ጣቢያው በሚገኙ የመከላከያ መሳሪያዎችም ላይ የፍተሻ ሥራ መከናወኑንም ይጠቅሳሉ።

በተቋሙ ሕብረት ስምምነት መሰረት መቀሌ ከሚገኘው ሪምና አጠቃላይ ሆስፒታል ጋር የሕክምናውል በመግባት የጣቢያው ሠራተኞች ሙሉ የሕክምና አገልግሎት እንዲያገኙ ተደርጓልም ይላሉ።በተጨማሪም ጣቢያው ከመቀሌ 25 ኪ.ሜ ርቆ ስለሚገኝ ተመላልሶ ለመመገብ አስቸጋሪ በመሆኑ ለብዙ ጊዜ ተዘግቶ የነበረውን የሠራተኛ ምግብ ቤት እንደገና በማደስና ተጓድለው የነበሩ እቃዎችን ከዋና መሥሪያ ቤት ጭምር በማስመጣት ምግብ ቤቱ ከነሐሴ ወር 2015 ዓ.ም መጀመሪያ ጀምሮ በተመጣጣኝ ዋጋ ለሠራተኛው አገልግሎት እየሰጠ እንደሚገኝ አቶ ካህሰ ይገልጻሉ።

በአጠቃላይ ከላይ ለአብነት የተነሱትን ጨምሮ ጣቢያው ከነበረበት ነባራዊ ሁኔታ አንጻር አፈጻጸሙ አበረታች መሆኑን የገለጹት አቶ ካህሰ በቀሪ ወራት ከተቋሙ የሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎች ጋር በመነጋገር የመለዋወጫ እቃዎችን፣ የሴፍቲ ማቴሪያሎች እና የሰው ኃይል እጥረትን ለመቅረፍ ይሠራል ይላሉ።

በአፈጻጸም ወቅት የታዩ ጠንካራ ጎኖችን በማጎልበት፣ ድክመቶችን ደግሞ በማረም ከዓመታዊ እቅዱ አንጻር የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ የተለየ ርብርብ እንደሚደረግም ይናገራሉ።ተቋሙ የመለዋወጫ ችግሩን ለመፍታት እና ኤፍዲ ከተባለ የፈረንሳይ ድርጅት ጋር በመነጋገር ሙሉ ተርባይኖችን ወደ ሥራ ለማስገባት በሂደት ላይ መሆኑን የገለጹት ኃላፊው የአሸጎዳ ንፋስ ኃይል ማመንጫ ጣቢያ የውሃ መስመር ቁፋሮ ቶሎ እንዲጀመርለትና የመንገድ ችግሩም እንዲቀረፍለት ይጠቁማሉ፡፡

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ለታዳሽ ኃይል ልማት ልዩ ትኩረት ሰጥቶ የንፋስ ኃይል ሀብትን በአግባቡ ለመጠቀም በአዳዲስ ቴክኖሎጂዎች በመታገዝ እንዲለማ እያደረገ ይገኛል።እንደሀገር ለታዳሽ ኃይል በተሰጠው ትኩረት አበረታች ለውጥ እየታየ ሲሆን ከታዳሽ ኃይል ማመንጫዎች የሚገኘውን አቅም ለማሳደግም በትኩረት እየተሠራ ነው።

በዚህም አሸጎዳን ጨምሮ አዳማ አንድና ሁለት፣ አይሻ ሁለት ፣ በግንባታ ላይ ያለው የአሰላ የንፋስ ኃይል ማመንጫዎች የኢትዮጵያን የታዳሽ ኃይል አቅም በማስፋት በአጠቃላይ ወደ 544 ሜጋ ዋት ከፍ እንዲል የሚያስችሉ ናቸው።ይህም ከውሃ የሚገኘው አብዛኛው የሀገሪቱ ኃይል በውሃ መቀነስና በጥገና ምክንያት መዋዠቅ ሲያጋጥመው ለማገዝ አቅም የሚፈጥር ነው።የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ለታዳሽ ኃይል ከሰጠው ትኩረት አንጻር በቀጣይም በርካታ የንፋስ ኃይል ማመንጫዎችን የመገንባት እቅድ እንዳለው የተቋሙ መረጃዎች ያመላክታሉ።

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ